2024 -2025 በጀት ዓመት የአፈጻጸም ሪፖርት

mebamfi.com.et

መባዕ ማይክሮ ፋይናንስ
ቀዳሚ የፋይናንስ አጋርዎ!

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት

mebamfi.com.et

መባዕ ማይክሮ ፋይናንስ
ቀዳሚ የፋይናንስ አጋርዎ!

እ.ኤ.አ የ2024/25 የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም

መግቢያ

የተከበራችሁ የመባዕ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ. ባለአክሲዮኖች፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተወካዮች፣ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ተወካዮች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላችሁ ክቡራን እንግዶች፣ ክቡራንና ክቡራት እንኳን ለመባዕ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ 2ኛ መደበኛ እና 2ኛ አስቸኳይ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሰላም መጣችሁ ማለት እወዳለሁ!

መባዕ ማይክሮ ፋይናንስ በ1,002 ባለአክሲዮኖች በመላው ኢትዮጵያ የማይክሮ ፋይናንስ ሥራ ለመስራት በማለም ዋና ገንዘብ /መነሻ ካፒታል/ ብር 17,194,000 (አስራ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና አራት ሺህ) በማዋጣት የቋቋሙት ሲሆን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሚያዚያ 30 ቀን 2016 ዓ.ም የሥራ ፈቃድ በማግኘት፥ ሐምሌ 29 ቀን 2016 ዓ.ም የኦፐሬሽን ሥራ ማስጀመሪያ ፈቃድ አገኝቶ ሥራውን በይፋ መጀመሩ ይታወሳል፡፡ ለተከበረው ጠቅላላ ጉባኤ እ.ኤ.አ ከሐምሌ 1 ቀን 2024 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2025 ድረስ ያለውን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት እንደሚከተለው በዝርዝር አቀርባለሁ፡፡

1. የኦፐሬሽን አፈፃፀም

በበጀት ዓመቱ በዓለም አቀፍ እና በሀገር ደረጃ በርካታ ተግዳሮቶች የታዩበት ሁኔታ ቢኖርም መባዕ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም እነዚህን ተግዳሮቶች በመቋቋም ለተጠናቀቀው በጀት ዓመት የተቀመጡ ዓላማዎችን ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የቆየ ሲሆን የአፈጻጸም ዝርዝሩም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1.1. የተቀማጭ ገንዘብ አፈጻጸም

እ.ኤ.አ ሰኔ 30/2025 በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የማይክሮ ፋይናንሱ አጠቃላይ ተቀማጭ ሒሳብ ብር 27,433,544.31 (ሃያ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ ሦስት ሺህ አምስት መቶ አርባ አራት ከ31 ሣንቲም) ደርሷል፡፡ ከዚህ ተቀማጭ ገንዘብ ውስጥ ብር 4,117,488.37 (አራት ሚሊዮን አንድ መቶ አስራ ሰባት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ስምንት ከ37 ሣንቲም) የሚሆነው የግዴታ ቁጠባ፣ ብር 10,184,955.94 (አስር ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አምስት ከ94 ሣንቲም) የሚሆነው የፍቃደኝነት ተቀማጭ ሲሆን ብር 13,131,100 (አስራ ሦስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ አንድ መቶ) የሚሆነው ደግሞ የጊዜ ገደብ ቁጠባ ነው::

1.2. የብድር ስርጭት አፈፃፀም (Loan Disbursement)

መባዕ ማይክሮ ፋይናንስ የደንበኞችን ፍላጎት ለማርካት 11 የብድር አይነቶችን ማለትም ለአነስተኛ ንግድ ብድር በግል እና በቡድን ፣ ለፍጆታ ብድር በቡድን እና በግል፣ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ብድር፣ ለአጭር ጊዜ ብድር፣ የቤት እድሳትና የግንባታ ብድር፣ ለቋሚ ንብረት ግዥ እና ለአጭር ጊዜ ብድር በማዘጋጀት በሦስቱም ቅርንጫፎች ብድሮችን አሰራጭቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በበጀት ዓመቱ ብር 38,748,000 (ሰላሳ ስምንት ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ ስምንት ሺህ) የብድር ስርጭት ለ392 (ሦስት ዘጠኝ ሁለት) ተበዳሪዎች ተፈጽሚል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2025 ላይ የተቋሙ ብድር ሚዛን አፈጻጸሙ በ357 ተበዳሪዎች ብር 30,680,187.17 (ሰላሳ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ሺ አንድ መቶ ሰማንያ ሰባት ከ17 ሣንቲም) ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ተቋሙ ከ11 የብድር አይነቶች ውስጥ ባለው አነስተኛ የካፒታል መጠን ምክንያት ለአንድ ተበዳሪ የሚሰጠው ብድር ውስን በመሆኑ አብዛኛው የብድር ሥርጭት የሚገኘው በፍጆታ ላይ ሲሆን፣ ትላልቅ ብድር የሚጠይቁ የግል ቢዝነስ ብድር፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ብድር፣ የቋሚ ንብረት ግዥ ብድር እና የአጭር ጊዜ ብድር ላይ በሥፋት መሥራት አልተቻለም፡፡ መባዕ ማይክሮ ፋይናንስ በቀጣይ አክስዮን በመሸጥ እና ካፒታሉን በማሳደግ ከላይ በተዘረዘሩት የብድር አይነቶች ላይ በትኩረት ለመሥራት አቅጣጫ በመያዝ ቅድመ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

1.3. የብድር ስርጭት ጥራት (Portfolio Quality)

በበጀት ዓመቱ በተቋሙ ውስጥ ምንም ውዝፍ ብድሮች እንዳይኖሩ ለማድረግ በብድር አመላለስ እና ጥራት ላይ የዲሬክተሮች ቦርድ በየወሩ እንዲሁም በየሩብ ዓመቱ እየገመገመ ለተቋሙ ሥራ አመራር አካላት አቅጣጫ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ደንበኞች ብድር ከመውሰዳቸው በፊት የሚፈለግባቸውን መስፈርቶች ማሟላታቸውንና ለብድር አመላለሱ በቂ ዋስትና ስለማቅረባቸው በየደረጃው ያለው የብድር ስርጭት ኮሚቴ ክትትል እና የማያቋርጥ ድጋፍ በማድረግ የተቋሙን የብድር ጥራት መጠበቅ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም የተበዳሪዎችን ሁኔታ በቅርበት በመከታተል እና ብድር ከመበላሸቱ በፊት በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃዎችን በመውሰድ ለተበዳሪዎች የተሰጡ ብድሮች ውዝፍ ውስጥ እንዳይገቡ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት የተሰጡ ብድሮች ከ99.999% በላይ ጤናማ ብድሮች ሲሆኑ 0.001% የሚሆን ትኩረት የሚያስፈልገው ብድር ይሆናል::

1.4. አዳዲስ ደንበኞች ምልመላ እና ቅርንጫፍን ማስፋፋት፣

መባዕ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አዳዲስ ደንበኞች ምልመላ እና የቅርንጫፍ ማስፋፋት ሥራዎችን የሠራ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ አራት ኪሎ፣ ሰአሊተ ምሕረት እና ጀሞ ሚካኤል አካባቢ ቅርንጫፎችን በመክፈት ለደንበኞች ተደራሽ ለመሆን ችሏል:: በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ 2,674 ቆጣቢ እና 392 ተበዳሪዎችን በአጠቃላይ 3,066 አዳዲስ ደንበኞችን ማፍራት ችሏል፡፡

1.5. የሰው ኃይል አደረጃጀት፤

በበጀት ዓመቱ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች ዋነኛው ተቋሙን ብቃት ባለው የሰው ኃይል ማደራጀት ነው፡፡ በዚህም መሠረት 19 የተለያዩ ሙያ ያላቸው ሠራተኞች ለመቅጠር የተቻለ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 11 የሚሆኑት ሴቶች ናቸው:: የሰው ኃይሉን አቅም በመገንባት ውጤታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ እና በብቃት ለመሥራት የሚረዱ የተለያዩ ሥልጠናዎች ለሠራተኞች ተሰጥቷል፡፡ የሰው ኃይል ውጤታማነት ለተቋም ትርፋማነት ወሳኝ በመሆኑ የሠራተኞችን የመፈጸም አቅም በማሳደግ፣ ዕቅድ መስጠት እና አፈፃፀማቸውን በወቅቱ የመገምገም ሥራ በትኩረት እየተሠራ ሲሆን የሰው ኃይል አፈጻጸም መለኪያ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል የአፈፃፀም መመሪያም በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

2. የፋይናንስ እና የአስተዳደር ሥራዎች

2.1. የፋይናንስ ሥራ አፈፃፀም

የተቋሙ የፋይናንስ ሪፖርት በዓለም አቀፍ የሂሳብ ምርመራ ደረጃዎች (IFRS) መሠረት የተዘጋጀ ሲሆን እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡

2.1.1. የሀብት እና ዕዳ መግለጫ

2.1.2. የሀብት መግለጫ

እ.ኤ.አ በሰኔ 30/2025 ላይ ጠቅላላ ሀብት ብር 50,747,633 (ሃምሳ ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ሦስት) የደረሰ ሲሆን ከባለፈው ዓመት ብር 12,145,589 (አስራ ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ አምስት ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ) አንፃር ሲታይ የ76% (ሰባ ስድስት ከመቶ) ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ ጠቅላላ ሀብቱ ከፍተኛ ለውጥ ያሳየበት ምክንያት በበጀት ዓመቱ ተቋሙ የብድር ሥርጭት በማድረጉ ሲሆን በደንበኞች እጅ የሚገኘው የተመላሽ ብድር መጠን ብር 30,680,187 (ሰላሳ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ሰባት) በመሆን ይህም ከጠቅላላ ሀብት 60 ከመቶ ድርሻ ይዟል፡፡

2.1.3. የዕዳ መግለጫ

የተቋሙ ጠቅላላ ዕዳ ብር 39,900,832 (ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ሰምንት መቶ ሰላሳ ሁለት) ሲሆን ከዚህ መካከል ብር 37,433,545 (ሰላሳ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ ሦስት ሺህ አምስት መቶ አርባ አምስት) 69 በመቶው የደንበኞች ቁጠባ ሲሆን ብር 10,000,000 (አስር ሚሊዮን) 25 ከመቶው ደግሞ ከባንክ የተገኘ ብድር ነው፡፡

2.1.4 ጠቅላላ ዕዳ እና ካፒታል

የተቋሙ ጠቅላላ ዕዳና ካፒታል ብር 50,747,633 (ሃምሳ ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ሦስት) የደረሰ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ከላይ የተገለጸው ብር 39,900,832 (ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ሰምንት መቶ ሰላሳ ሁለት) የተቋሙ ዕዳ ነው፡፡ እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2025 ላይ የተቋሙ ጠቅላላ ዕዳ እና ካፒታል ከፍተኛ ለውጥ ያሳየበት ምክንያት ከደንበኞች የተሰበሰበ የቁጠባ መጠን ከፍተኛ መሆን እንዲሁም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 10 ሚሊዮን ብድር መገኘቱ ዋነኞቹ ምክንያቶች ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት የተቋሙ የተጣራ ካፒታል ብር 10,846,801 (አስር ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ አንድ) ሆኗል፡፡

2.1.5 ትርፍ/ኪሳራ

2.1.5.1 ገቢ

የበጀት ዓመቱን የገቢ አፈፃፀም ስንመለከት ብር 4,975,672 (አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ሁለት) ሲሆን ይህም በገቢ ርዕስ በዝርዝር ሲታይ ከብድር ወለድ ብር 3,712,528 (ሦስት ሚሊዮን ሰባት መቶ አስራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ስምንት)፣ ከአገልግሎት ክፍያ ብር 1,202,990 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና) እና

ከሌሎች ምንጮች ብር 60,154 (ስድሳ ሺህ አንድ መቶ ሃምሳ አራት) ገቢ ተገኝቷል፡፡ የገቢ አፈፃፀም ዝቅተኛ እንዲሆን አስተዋጽዖ ካደረጉ ጉዳዮች መካከል በብድር ገንዘብ እጥረት ምክንያት የብድር ስርጭት ዝቅተኛ መሆን በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ለብድር አገልግሎት የሚሆን ገንዘብ በቁጠባ ለመሰብሰብ ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ የነበረ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች በቂ ቁጠባ መሰብሰብ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተቋሙ የብድር ሥርጭት ፍላጎት ለማሟላት ወደ ኮሜርሻል ብድር አማራጭ ገብቷል፡፡

የተከበራችሁ ባለአክሲዮኖች ኮሜርሻል ብድርን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ብር 10 ሚሊዮን የተገኘ ሲሆን ለብድር ስርጭት አገልግሎት ላይ የዋለው እ.ኤ.አ ሐምሌ ወር 2025 መጀመሪያ ጀምሮ በመሆኑ የተገኘው ብድር ለተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ሊሆን አለመቻሉን ለዚህ ጠቅላላ ጉባኤ መግለጽ እንወዳለን፡፡

2.1.5.2 ወጪ

በበጀት ዓመቱ ለአስተዳደራዊ እና ለጠቅላላ አገልግሎት ማለትም ለሠራተኛ ደመወዝ ብር 5,499,449 (አምስት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ አርባ ዘጠኝ)፣ ለቢሮዎች ኪራይ ብር 1,601,460 (አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ አንድ ሺህ አራት መቶ ስድሳ)፣ ለቋሚ ንብረት እርጅና ቅናሽ 220,372 (ሁለት መቶ ሃያ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ሁለት)፣ ለቁጠባ ወለድ 1,073,652 (አንድ ሚሊዮን ሰባ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሳ ሁለት)፣ የብድር መጠባበቅያ 19,123 (አስራ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሃያ ሦስት) እንዲሁም ለሌሎች ለኦፕሬሽናል ሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ብር 1,597,810 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ ስምንት መቶ አስር) ሲሆን በድምሩ ብር 10,011,866 (አስር ሚሊዮን አስራ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ስድሳ ስድስት) ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ከወጪዎቹም መካከል በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች አስገዳጅ ሕግ ምክንያት ብድር ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የብድር መጠባበቂያ ወጪ ተብሎ ብር 19,123 (አስራ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሃያ ሦስት) የተመዘገበ ሲሆን ወጪን ለመቀነስ ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ የቆየ ቢሆንም የቢሮ መገልገያ ቁሳቁሶች፣ የህትመት ዋጋ፣ ቋሚ ንብረት እና የተለያዩ የአገልግሎቶች ወጪ ላይ ያለው የዋጋ ንረት ከዕቅድ በላይ መሆኑ በዋናነት የሚጠቀስ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በገቢና በወጪ ርዕሶች በዝርዝር በተገለጸው መሠረት በበጀት ዓመቱ ተቋሙ ብር 5,036,195 (አምስት ሚሊዮን ሰላሳ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና አምስት) ኪሳራ ለማስመዝገብ ተችሏል።

3. የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት እና በቴክኖሎጂ ማዘመን፣

ከመባዕ ማይክሮ ፋይናንስ ዓላማዎች አንዱ ዘመኑ ባፈራቸው ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ዲጂታል የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት አንዱ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሠረት ዓላማውን እውን ለማድረግ የተለያዩ የሀገር ውስጥ እና የውጪ ድርጅቶችን በማወዳደር Core Banking አገልግሎት መስጠት የሚችል ድርጅት መለየት ተችሏል፡፡ ነገር ግን የተቋማችን ካፒታል አነስተኛ በመሆኑ ተግባራዊ ማድረግ ያልተቻለ ሲሆን የአክሲዮን ሽያጭ ሲጀመር Core Banking ወደ ትግበራ እንዲገባ የዶክመንት ዝግጅቱ ተጠናቆ ይገኛል፡፡

4. የአክሲዮን ሽያጭ ላይ የተሠሩ ሥራዎች፤

የመባዕ ማይክሮ ፋይናንስ 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የተቋሙን ካፒታል ወደ 300 ሚሊዮን ለማሳደግ መወሰኑ ይታወሳል፡፡ የዳሬክተሮች ቦርድ ከተቋሙ ሥራ አመራር ጋር በመሆን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ከኢትዮጵያ ካፒታል ገባያ ባለሥልጣን ጋር ካፒታሉን ለማሳደግ የሚያስችል ተደጋጋሚ ውይይቶች ተከናውነዋል፡፡ በዚህም መሠረት በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ለመመዝገብ አማካሪ ድርጅት በመቅጠር የምዝገባ ሂደቱ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡

5. ያጋጠሙ ችግሮች

5.1. አክስዮን ሽያጭ ማድረግ አለመቻል

የተከበረው ጠቅላላ ጉባኤ እንደሚያስታውሰው በ1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የተቋሙን ካፒታል ወደ 300 ለማሳደግ ተወስኖ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ነገር ግን በፈራሚዎች ጉባኤ ያልተገኙ እና በኋላ በተደረገ የማጣራት ሥራ አክስዮን የገዙ እና መረጃ ያሟሉ ባለአክሲዮኖችን በ1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በበላአክስዮንነት እንዲመዘገቡ በተወሰነው መሠረት ለማስፈጸም እና ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ለማግኘት የነበረ መጓተት፣ የ1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባኤን ላማጽደቅ ከስድስት ወራት በላይ ወስዷል፡፡ የቦርድ አባላትም ለብሔራዊ ባንክ ከፍተኛ ኃላፊዎች ጉዳዩን በማቅረብ ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ ባደረገው ጥረት በመጨረሻም ከብሔራዊ ባንክ ይሁንታ ተገኝቶ በውልና ማስረጃ የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የያዘው ቃለ ጉባኤ እንዲጸድቅ ሆኗል። ይኸም ሂደት እንዳለቀ አክሲዮን ለመሸጥ በተዘጋጀንበት ወቅት አዲስ የወጡ የካፒታል ገበያ መመሪያዎች፣ በትራንዛክሽን አድቫይዘር በኩል ካልሆነ አክሲዮን መሸጥ አለመቻላችን ሌላው እንቅፋት ሆኖብናል። ይኸንንም ለማስጠናት በወቅቱ በትራንዛክሽን አድቫይዘር ድርጅቶች የተጠየቅነው ከ9 ሚሊዮን ብር በላይ በመሆኑና ተቋማችን ይኸንን ገንዘብ መክፈል ባለመቻሉ ምክንያት ሥራውን ማሠራት ሳይችል የቆየ ቢሆንም አሁን ላይ በ1.9 ሚልየን ብር ለማሠራት ስምምነት ተደርጎ ሂደቱ ተጀምሯል፡፡

በዚህ ምክንያት የአክሲዮን ማኅበሩ ዋና ተግዳሮት አነስተኛ ካፒታል በመሆኑ ከኪሳራ ወጥቶ ትርፋማ ሊያደርግ በሚችል ደረጃ ሥራውን ማስፋት አልተቻለም።

5.2. የሠራተኞች ፍልሰት

በኢንዱስትሪው የሚገኙና እየገቡ ያሉት ተመሳሳይ ተቋሞች ከፍተኛ ካፒታል የያዙ በመሆናቸው በአንጻሩ መባዕ ማይክሮ ፋይናንስ በአነስተኛ ካፒታል እየሠራ በመሆኑ በዘርፉ ያለው ውድድር በርካታ ጉዳዮች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ ተቋማችን ካለው አቅም እና ካፒታል አነስተኛነት የተነሳ ለሠራተኞቹ በቂ እና ከሌሎች አቻ ተቋማት ጋር ሊወዳደር የሚችል ደመወዝ መክፈል ባለመቻሉ የሠለጠኑ እና ብቁ የሆኑ ሠራተኞች ተቋሙን ለቀዋል፡፡

5.3. የብድር ገንዘብ እጥረት

መባዐ ማይክሮ ፋይናንስ ከሌሎች ተመሳሳይ/አቻ ተቋማት አኳያ ሲታይ ወደ ሥራ ሲገባ በእጅጉ አነስተኛ የመስሪያ ካፒታል በመያዝ ከመሆኑ ባሻገር ለከፈታቸው ቅርንጫፎች ለካፒታልና ፍጆታ ዕቃዎች ከፍተኛ ወጪዎችን በማውጣቱ ለብድር አገልግሎት የሚሆን በቂ ገንዘብ ሊኖረው አልቻለም፡፡

ይኼን ችግር ለመቅረፍ በቁጠባ ወይም በአክሲዮን ሽያጭ እንዲሁም ከግል ባንኮች ተጨማሪ ብድር ለማግኘት ከፍተኛ ርብርብ የተደረገ ቢሆንም በሚፈለገው ልክ ሊሳካ አልቻለም፡፡

5.4. የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ሁኔታ (የኑሮ ውድነት)

በሀገሪቱ ያለው የኑሮ ውድነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄዱ በብድር ሆነ በቁጠባ ላይ ከፍተኛ የአፈፃፀም ክፍተት አስከትሏል፡፡

5.5. የተቋሙ የብድር መጠን ማነስ

በበጀት ዓመቱ የተቋሙ ካፒታል የብድር ጣሪያ ለአንድ ደንበኛ እስከ 100 ሺህ ብር ብቻ በመሆኑ ደንበኞች ወደ ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት እየሄዱ መሆኑ ሌላው የተቋሙ የኦፐሬሽን ሥራ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል፡፡

6. ላጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

- በበጀት ዓመቱ ተቋሙ ያለበትን የገንዘብ ዕጥረት ለመቅረፍ ከተለያዩ የግል ባንኮች ብድር ተጠይቆ ከአንድ ባንክ 10 ሚሊየን ለማግኘት ተችሏል፣
- ከአሐዱ ባንክ ጋር የመግባቢያ ስምምነት በመፈረም የሥራ ማስኬጃ ብድር ለተያዘው በጀት ዓመት ለማግኘት ተችሏል።
- ቁጠባ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ ሰፊ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፣
- ከተለያዩ ተቋማት ጋር አጋርነት በመፍጠር ሥራዎች ተሠርተዋል፣
- የተቋሙን የብድር መጠን ለማሳደግ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ከኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ጋር ተደጋጋሚ ውይይት በማድረግ የአክሲዮን ሽያጭ ቅድመ ሁኔታዎች ተከናውነዋል፣

7. የትኩረት አቅጣጫዎች

- በሂደት ላይ የሚገኘውን የአክሲዮን ሽያጭ በተያዘለት እቅድ በማከናወን በአጭር ጊዜ ውስጥ አክሲዮን በመሸጥ የተቋሙን ካፒታል፤
- የተለያዩ ስልታዊ እቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣
- በተያዘው በጀት ዓመት የኮር ባንኪንግ ሥራ በቅርንጫፎች ላይ ሙሉ በሙሉ በማስጀመር የተቋሙን አሠራር ማዘመን፣
- የተቋሙን ሠራተኞች አቅም በሥልጠና በማገዝ ውጤታማነታቸውን ማሳደግ፤

  በአጠቃላይ ተቋሙ ምርታማ እና ትርፋማ እንዲሆን የሚያስችሉ አሠራሮችን መዘርጋት እና መተግበር፤

ማጠቃለያ

ከላይ የተጠቀሱት ተግዳሮቶች ቢኖሩም፣ ተቋማችን ራእያችንንና ተልዕኮአችንን ለማሳካት የጀመርነውን ጉዞ በጽኑ እምነትና በቁርጠኝነት እያስቀጠለ መሆኑን በእርግጠኝነት እናረጋግጣለን። ማይክሮፋይናንስ ተቋማችን በአደረጃጀት፣ በቅርንጫፍ መስፋፋት፣ ከአጋሮች ጋር በሚጠናከረው ትብብር እና በደንበኞች አገልግሎት ዘርፍ ያሳየው ቀጣይነት ያለው እድገት የተቋሙ መሠረት መጠናከሩንና ወደፊት የሚጠበቀውን ተስፋ ያሳያል። ባለፈው ዓመት ውስጥ ከወር ወር እየተሻሻለ የመጣው አፈጻጸም ይህንን አዎንታዊ አቅጣጫ በግልጽ ያረጋግጣል።

ውድ ባለአክሲዮኖቻችን፣ የተቋሙን ካፒታል ወደ 300 ሚሊዮን ብር ለማሳደግ የወሰናችሁትን ውሳኔ ወደ ተግባር የምንቀይርበት ወሳኝና ተስፋ ሞላ ምዕራፍ ላይ እንገኛለን። በመጪው ጊዜ የአክሲዮን ሽያጫችንን በማስፋፋት፣ የታቀዱ ቅርንጫፎችን በመክፈት፣ የቁጠባ ማሰባሰብ ዘመቻዎችን በማጠናከር እና የብድር አገልግሎታችንን በመስፋፋት የተቋሙን ዕድገትና ትርፋማነት በጽኑ መሠረት ላይ ለማቆም በተወሰነ ዕቅድ እየሰራን እንገኛለን።

በዚህ ሂደት፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ አስተዳደሩ እና መላው ሰራተኞች በአንድነት ተቀናጅተው በከፍተኛ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት እየሰሩ መሆናቸውን እናረጋግጣለን። ስለዚህም ክቡር ባለአክሲዮኖቻችን በአክሲዮን ግዥ፣ በቁጠባ ማሰባሰብ እና በብድር መሳተፍ ዘርፎች ያላችሁትን ያልተቋረጠ ድጋፍና ትብብር በመቀጠል ለተቋማችን የተሻለ ወደፊት እንድንገነባ በእምነትና ተስፋ አብረን እንድንጓዝ በአክብሮት እንጠይቃለን።

በትዕግስት እና በትኩረት ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ!

የመባ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማኅበር ቦርድ

ኢትዮጵያ

አዲስ አበባ

***ታኅሣሥ* 11 ቀን 2018 ዓ.ም**

መባዕ ማይክሮ ፋይናንስ አ.ማ

Meba Microfinance S.C

መባዕ ማይክሮ ፋይናንስ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች፦

የቁጠባ አገልግሎት

ሀ. የፈቃደኝነት ቁጠባ

1. የግል ቁጠባ
2. የሴቶች ቁጠባ
3. የሕጻናትና ታዳጊ ልጆች ቁጠባ
4. የሳጥን ቁጠባ
5. የድርጅቶች ቁጠባ
6. ከወለድ ነጻ ቁጠባ
7. የአዛውንቶች ቁጠባ
8. የልዩ ዓላማ ቁጠባ

ለ. የጊዜ ገደብ ቁጠባ

የብድር አገልግሎት

1. የንግድ ብድር
2. ኢንተርፕራይዝ (SME) ብድር
3. የፍጆታ ብድር
4. ቋሚ ንብረት ግዢ ብድር
5. ልዩ የአጭር ጊዜ ብድር
6. የቁጠባ ዋስትና ብድር
7. የግብርና ብድር
8. አግሪ -ቢዝነስ ብድር